በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200555

ቀን፡-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ መሐመድ አበራ- አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ታጁ ጌታዬ

2. ሀሰን አሊ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ተጠቃሚነት መብት የሚመለከት ነዉ፡፡በስር በወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት ተዋበች አስናቀዉ ከሳሽ የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ በዚህ መዝገብ ላይ በተከራካሪነት ያልተሰየሙት ካሳዉ መንግስቱ 2ኛ ተከሳሽ የአሁን ጣልቃ ገቦች ከሌሎች ስድስት ጣልቃ ገቦች ጋር በመሆን በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡ የክሱም ይዘት በወረዳዉ 02 ቀበሌ ዉስጥ በክሱ በተጠቀሱት አዋሳኞች የሚታወቅ በ1983ዓ/ም የተመራሁበትንና በደብተር ያስመዘገብኩትን 4 ገመድ የእርሻ መሬት አመልካች ይዞብኝ ለስር 2ኛ ተከሳሽ በመሸጡና 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሊገነባ ስለሆነ የያዙብኝን መሬት እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ መሬቱ የከሳሽ ሳይሆን ከሟች አሊ ፈለቀ ጋር በ1983ዓ/ም አብረዉ ተመርተዉ አቶ አሊ ፈለቀ በ2003ዓ/ም ሲሞት እኔ ከሟች ጋር በቤተሰብ አባልነት አብሬ ያደኩ በመሆኔ ወራሽነቴን አረጋግጬ ለሁለት ከከሳሽ ጋር ሁለት ሁለት ገመድ ተካፍለናል፡፡በደረሰኝ መሬት ላይ ቤት ልሰራ እንጨትና ድንጋይ አራግፌያለሁ እንጂ የከሳሽን አልነካሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽም መሬቱን አልገዛሁም፤የአሁን አመልካች ቤት ሊሰራ ነዉ በማለታቸዉ ድንጋይና እንጨት አራግፌያለሁ በማለት ለክሱ መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ክስ የተመሰረተበት መሬት የሟች አባታችን አሊ ፈለቀ ሲሆን የአሁን አመልካች 2 ገመድ መሬት መብት ሳይኖራቸዉ በመያዝ ለሌላ ሰዉ በሽያጭ አስተላልፈዉ ቤት ሊያሰሩበት ስለሆነ ወርሰን የያዝነዉን መሬት እንዲያስረክበን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡በዚህ የጣልቃ ገቦች አቤቱታ ላይ የስር ከሳሽ በሰጡት መልስ መሬቱ የጣልቃ ገቦች መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ የሟቹ የቤተሰብ አባል በመሆን ወራሽነቴን አረጋግጬ የያዝኩት ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 28616 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ በቀን 12/05/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለክርክሩ መነሻ ከሆነዉ 4 ገመድ መሬት ዉስጥ 2 ገመድ መሬት የሟች አሊ ፈለቀ እንደሆነና አመልካች የሟች የአቶ አሊ ፈለቀ የቤተሰብ አባል በመሆን መሬቱን ሊይዙ እንደቻሉ በማስረጃ ስለተረጋገጠና ይሕም በአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 17/5 መሰረት የሕግ ድጋፍ ያለዉ በመሆኑ አመልካች መሬቱን በሕግ አግባብ ስለያዙ ሊለቁ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ጣልቃ ገቦች ከሌሎች የሥር ጣልቃ ገቦች ጋር በመሆን ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 45606 ላይ በቀን 18/05/2012ዓ/ም በሰጠዉ ብይን ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡

በመቀጠል ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-28591 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 07/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክርክሩ አዲሱ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ተፈጻሚ በሆነበት ጊዜ የተጀመረ እና በቀድሞዉ አዋጅ መሰረትም ተወርሶ ሕጋዊ መብት የተቋቋመበት ስላልሆነ በአሁን አዋጅ መሰረት ቅድሚያ ሊወርስ የሚገባዉ ማነዉ?የሚለዉ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት ጭብጥ ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 መሰረት የሟች መሬት በቅድሚያ ለመዉረስ መብት ያለዉ የሟች ልጆች ሲሆኑ ልጆች ሞተዉ ከሆነ ደግሞ የልጅ ልጅ ምትክ ሆነዉ እንዲወርሱ ሊደረግ የሚቻል ስለመሆኑ በንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪዎችም የቀድሞ አዋጅ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ወራሽነታቸዉን ያሳወጁ ቢሆንም ቀድመዉ ወርሰዉ ያልያዙ በመሆኑ በአሁን አዋጅ የሚስተናገድ ከመሆኑ አንጻር ከአሁን አመልካች ቀድመዉ የሟች አሊ ፈለቀን መሬት የመዉረስ መብት ያላቸዉ የአሁን ተጠሪዎች ስለሆኑ አመልካች የሟችን ሁለት ገመድ መሬት ለተጠሪዎች ሊያስረክብ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 27/04/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ለክሱ መነሻ ከሆነዉ መሬት የስር ከሳሽ ድርሻቸዉን መዉሰዳቸዉ ከመረጋገጡም በተጨመሪ ክሳቸዉን በማስረጃ ባለማስረዳታቸዉ ክሱ ዉድቅ መደረግ ነበረበት፡፡ለተጠሪዎች(ለጣልቃ ገቦች) ሕጉ የወራሽነት መብት የሚጠብቅ ቢሆንም ተጠሪዎች የራሳቸዉ የሆነ መሬትና መተዳደሪያ ደንብ ያላቸዉ ሲሆኑ በአንጻሩ አመልካች ከሁለት ዓመቶ ጀምሮ እዚያዉ አድጌ አያቴ አቶ አሊ በሞት እስከተለዩበት 2003ዓ/ም ኖሬ ያደኩኝ ነኝ፡ለመሬቱ በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤያለሁ፡፡አያቴ ከሞቱበቱ በኋላ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ በስሜ ግብር እየገበርኩ እገኛለሁ፡፡የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 የራሱ የሆነ መሬት የሌለዉ የቤተሰብ አባል መሬቱን በቅድሚያ እንዲወርስ መብት የሚሰጥ ነዉ፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቤተሰብ አባል መሆኔ ተረጋግጦ እያለ የያዝኩትን መሬት እንዲለቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች መሬቱን የያዙት የቤተሰብ አባል በመሆን በሕጋዊ መንገድ ነዉ ተብሎ የተወሰነዉን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመዉረስ መብት የላቸዉም በማለት የሻረበትን አግባብነት ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 26/09/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1983 ዓ/ም የተደለደለዉ ለሟች አቶ አሊ ፈለቀ እና ለስር ከሳሽ ወ/ሮ ተዋበች አስናቀዉ ነዉ፡፡ሆኖም አቶ አሊ ፈለቀ ከሞቱ በኋላ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ 1ኛ ተ|ጠሪ እናቴን ወ/ሮ ዘነበች አሊን በመተካት እንዲሁም ሁለተኛ ተጠሪ የወላጅ አባቴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔን ከሌሎች ወራሾች ጋር በማረጋገጥ መሬቱን ከስር ከሳሽ ጋር በመሆን አከራካሪዉን መሬት ስንጠቀም ቆይተናል፡፡በ2011ዓ/ም ወ/ሮ ተዋበች አስናቀዉ ሰባት ሰዎች በሚል የመሬት ማረጋገጫ ደብተር በስማችን አዉጥተን እየተጠቀምን እንገኛለን፡፡ክርክሩ የተጀመረዉ የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ጸድቆ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ በመሆኑ፣አመልካች በመሬቱ ላይ ቀድመዉ የመሬት ባለይዞታነት ደብተር በማዉጣት ያቋቋሙት መብት ባለመኖሩ፣አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 ላይ ባስቀመጠዉ የወራሽነት ቅደም ተከተል መሰረት የቀድሞዉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 16/5 እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣዉን ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 ስለወራሽነት ቅደምተከተል አካሄድ ለዉጦ ቅድሚያ መዉረስ የሚገባዉ የቤተሰብ አባል ሳይሆን የሟች ልጆች ናቸዉ በማለት ደንግጓል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅድሚያ የመዉረስ መብት ያላቸዉ የሟች ልጆች ናቸዉ በማለት የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻሩና አመልካች መሬቱን እንዲለቁ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ በማሻሻል የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ለአመልካች አይገባቸዉን በማለት ሲወስኑ ለጉዳዩን

ተገቢዉን ሕግ መሰረት በማድረግ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በመያዝ በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የስር ከሳሽ ወ/ሮ ተዋበች አስናቀዉ በክሱ የተጠቀሰዉና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ 4 ገመድ መሬት በአጠቃለይ የእሳቸዉ እንደሆነ በመግለጽ አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲለቁላቸዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች እና ሌሎች አራት ሰዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጣልቃ ገብነት መከራከራቸዉን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ከቀረበዉ ክርክርና ማስረጃዎች ለክሱ መነሻ ከሆነዉ ስፋት 4 ገመድ ከሆነ መሬት 2 ገመድ የስር ከሳሽ ይዞታ እንደሆነ ቀሪዉ ግማሽ መሬት ደግሞ የሟች አቶ አሊ ፈለቀ ይዞታ እንደሆነ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠና በግራ ቀኙም የታመነ ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች የሟች ቤተሰብ አባል እንደሆኑና የስር ጣልቃ ገቦችን ጨምሮ የአሁን ተጠሪዎች(የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሟች አቶ አሊ ፈለቀ ሚስት ወራሽ እንደሆኑ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት መልስ ላይ ገልጸዋል) የሟች አቶ አሊ ፈለቀ ወራሾች እንደሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ አከራካሪዉ የሟች አቶ አሊ ፈለቀ መሬት የሟቹ የቤተሰብ አባል ለሆኑት አመልካች ሊተላለፍ የሚገባ ሳይሆን ለአሁን ተጠሪዎች ሊተላለፍ የሚገባ ነዉ ተብሎ መወሰኑ እና ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የወጣዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 ሳይሆን የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ ሕግ በዜጎች መካከል ያለዉን ግንኙነት ለመቆጣጠር ሲባል በሕግ አዉጪዉ አካል የሚወጣ መሣሪያ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የሚወጣዉም ሕጉ በሥራ ላይ ባለበት ወቅት በዜጎች መካከል ያለዉን ወይም ወደ ፊት የሚፈጠረዉን ግንኙነት ለመቆጣጠር ወይም ለመዳኘት በመሆኑ ሕጉ ከመዉጣቱ በፊት ወይም ከተሻረ በኋላ በተፈጠረ/በሚፈጠር ግንኙነት ላይ ሕግን ተፈፃሚ ማድረግ አይቻልም፡፡ ይህም ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም ከሚለዉ አጠቃላይ መርህ (the principle of non-retroactivity of laws) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉም መርህ መሠረተ ሃሳቡም ሕጉ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለተፈጠረ መብትና ግዴታ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ተፈጻሚ መሆን ስላለበት እና ዜጎች በሚያዉቁት ሕግ መተዳደር አለባቸዉ የሚለዉን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡እንዲሁም አንድ ሕግ የሚጸናበትን ጊዜ አስመልክቶ በሕግ አዉጪዉ ከተደነገገዉ ቀን በፊት ለተፈጠሩት ክስተቶች ወይም መብትና ግዴታዎች ተፈፃሚነት አይኖረዉም የሚል ሃሳብ ያለዉ ነዉ፡፡ የዚህ መርህ ተግባራዊነት የሕግ የበላይነት ከሚረጋገጥባቸዉ መገለጫዎች መካከል አንዱ ነዉ፡፡ ስለሆነም አንድ መሠረታዊ ሕግ (substantive law) ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ሕግ አዉጪዉ በሕጉ ላይ በልዩ ሁኔታ ካላመላከተ በስተቀር ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ለያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን መሠረታዊ ሕግ ሲወስን መሠረት ሊያደርግ የሚገባዉ ወይም

መሠረት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በተፈጠረበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉን ሕግ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ተግባር (Juridical act) ወይም መብትና ግዴታ በተፈጠረበት ጊዜ የነበረዉ ሕግ በሌላ ሕግ የተተካ ሆኖ ሲገኝ እና ክርክሩ ለፍርድ ቤት ወይም ለዳኝነት ሰጪ አካል የቀረበዉ አዲሱ ሕግ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት ያለበት በመብትና ግዴታው በተፈጠረበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረው ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ ክርክሩ አዲሱ ሕግ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ጉዳዩ በአዲሱ ሕግ መሠረት እንዲመራ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን ማድረግ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉን የሕግ መርህ የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የሕግ የባላይነት እንዳይረጋገጥ ወይም እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ባለመብት አቶ አሊ ፈለቀ የሞቱት በ2003ዓ/ም መሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የገጠር መሬትን ወራሽነት መብትን የሚመለከት ሲሆን የወራሽነት መብት የሚተላለፍላቸዉን ሰዎች ማንነትና ቅደምተከተል አስመልክቶ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከተመለከተዉ ዉጭ ከዉርስ ጋር በተያያዘ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ላይ የተመለከቱ ደንቦች እና መርሆዎች ከገጠር መሬት ወራሽነት ጋር በተያያዘም እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት አላቸዉ፡፡ ዉርስ የሚከፈትበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 826/1 ስር እንደተደነገገዉ ዉርስ የሚከፈተዉ አዉራሹ በሞተበት ጊዜ እና ቦታ ነዉ፡፡ስለሆነም አንድ ሰዉ የሟች ወራሽ መሆን ያለመሆኑ የሚረጋገጠዉ ሟች በሞተበት ጊዜ በሥራ ላይ ያለዉን ሕግ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የወራሽነት ማረጋገጫ ከስሙም መገንዘብ እንደሚቻለዉ በሕግ የተገኘን መብት ለማረጋገጥ የሚሰጥ እንጂ በእራሱ መብት የሚሰጥ ስላልሆነ ዉርሱ ተከፈተ የሚባለዉ የወራሽነት ማረጋገጫ የተወሰደበት ጊዜ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡በዚህ መሰረት የአከራካሪዉ መሬት ባለመብት የሞቱት በ2003 ዓ/ም በመሆኑ በዚህ ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ ከቀን 21/09/1998ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን የጀመረዉ የተሻሻለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ከቀን 21/12/1998ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ የሆነዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 ናቸዉ እንጂ ከሐምሌ 2009ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን የጀመረዉ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አይደለም፡፡ በዚህ አዋጅ ቁጥር 252/2009 በመሸጋገሪያ ድንጋጌ በአንቀጽ 57 ላይ በሌሎች ሕጎች የተቋቋሙ መብቶች እና ግዴታዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ ተፈፃሚነታቸዉ እንደሚቀጥል እንዲሁም አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ እልባት ያገኛሉ በሚል መደንገጉ ከዉርስ ጋር በተያያዘ ለሚነሳ ክርክር ይህ አዋጅ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ እንዲሆን ተደንግጓል የሚያስብል አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በየደረጃዉ ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ነዉ በማለት ይህንን አዋጅ መሰረት አድርገዉ መወሰናቸዉ ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም በሚል የሚታወቀዉን ተቀባይነት ያለዉን የሕግ መርህ የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 7(1/ለ) ስር እንደተደነገገዉ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣዉ ደንብ ላይ በሚወሰነዉ መሰረት በክልሉ ዉስጥ ነዋሪ የሆነና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ የመሬት ይዞታ መብት በዉርስ የማግኘት መብት አለዉ፡፡በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 16/5 ላይ አንድ የመሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቱን በተመለከተ ሳይናዘዝ የሞተ ሰዉ መብቱ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ መተዳደር ለሚፈልግ የሟቹ ልጅ ወይም ቤተሰብ አባል ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገዉ ቅደም ተከተል መሰረት እንደሚተላለፍ ተደንግጓል፡፡ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በወጣዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 ስር ማንኛዉም የገጠር መሬት ባለይዞታ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ ወይም ኑዛዜዉ በሕግ ፊት የማይጸና የሆነ እንደሆነ የመሬት ይዞታዉ ለሟቹ የቅርብ ዘመዶች በዉርስ የሚተላለፍበት ቅደም ተከተል ተደንግጓል፡፡በዚህ ቅደም ተከተል መሰረት በአንቀጽ 11(7/ሀ) ላይ እንደተደነገገዉ በቀዳሚነት የመዉረስ መብት የተሰጣቸዉ ለአካለ መጠን ያልደረሱ የሟቹ ልጆች፣ልጅ ከሌለዉ የቤተሰብ አባላቱ እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡ከእነዚህ ሕግጋት አንጻር የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን መርምረዉ አከራካሪዉ መሬት ተጠሪ ሊለቁ የሚገባ መሆን አልመሆኑን በተመለከተ ዉሳኔ አለመስጠታቸዉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡በተጨማሪም ክሱን የመሰረቱት የስር ከሳሽ አመልካች መሬቱን እንዲለቁላቸዉ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ከተደረገና የአሁኑን ተጠሪዎች ጨምሮ የስር ጣልቃ ገቦች በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በመሆኑ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አንጻር የክርክሩ ዉጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉም ተገናዝቦ ታይቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ የሥነ ሥርዓት ጥያቄ ነዉ፡፡በመሆኑም በእነዚህ ጭብጦች ላይ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ስላልሰጡበት ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ተገቢዉን ሕግ ተግባራዊ ካለማድረግ እና ከክርክር አመራር አንጻር የተፈጸመዉ የሕግ ስህተት ታርሞ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28616 ላይ በቀን 12/05/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45606 ላይ በቀን 18/05/2012ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-28591 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 07/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የሟች አቶ አሊ ፈለቀ መሬት በቤተሰብ አባልነት አመልካች ይዘዉ ሊቀጥሉ የሚገባ ነዉ ወይስ ለወራሶች ሊተላለፍ ይገባል የሚለዉን ከአዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ከደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 መስፈርቶችና ቅደም ተከተል አንጻር በመመርመርና እነዚህ ሕግጋት ካስቀመጡት መስፈርቶች ጋር በተያያዘ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባ ፍሬ ነገር ካለም በማስረጃ በማጣራት ከላይ በፍርዱ ሀተታ ላይ የተጠቀሰዉን የሥነ ሥርዓት

ጥያቄ ከግምት በማስገባት ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር የወረዳ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እ ንዲጂዽ 7 / 7
ለ ፍርድ አፈጻጸምዓለ ማአያገለግልም